የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን
ETHIOPIAN HUMAN RIGHTS COMMISSION

በኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን የተዘጋጀ



Photo credit: EHRC/Department of Refugees, IDPs and Migrants' Rights/Surafel Dinkalem

# የስደተኞች እና ጥገኝነት ጠያቂዎች የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ የዘርፍ ሪፖርት

## አንኳር ጉዳዮች

www.ehrc.org

ታኅሣሥ 2016 ዓ.ም.

## አንኳር ጉዳዮች

የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን (ኢሰመኮ) የስደተኞች እና ጥገኝነት ጠያቂዎችን ሰብአዊ መብቶች ሁኔታ ላይ ትኩረት ሰጥቶ የክትትል እና ምርመራ ሥራዎችን ሲያከናውን የቆየ ሲሆን፤ በዚህም መረጃዎችን ለመሰብሰብ የተለያዩ ዘዴዎች በመጠቀም ሀገራዊ እና ዓለም አቀፋዊ ሕጎችን እንዲሁም የሰብአዊ መብቶች ስታንዳርዶችን/ደረጃዎችን መሠረት በማድረግ በተዘጋጁ የክትትል እና የምልከታ ቅጾች (መጠይቆች) መረጃ እና ማስረጃ አሰባስቧል፡፡

ኢትዮጵያ ስደተኞችን እና ጥገኝነት ጠያቂዎችን ተቀብላ ጥበቃ ለማድረግ ተግባራዊ ሊደረጉ የሚችሉ ዓለም አቀፍ፣ አህጉር አቀፍ እና ብሔራዊ የስደተኞች የሕግ ማዕቀፎች በሥራ ላይ እንዲውሉ አድርጋለች፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ሕጎች (International Human Rights Law) እና ዓለም አቀፍ የሰብአዊነት ሕጎች (International Humanitarian Laws) የስደተኞችን እና ጥገኝነት ጠያቂዎችን መብቶች ለመጠበቅ ተግባራዊ ይደረጋሉ፡፡

በኢትዮጵያ ለሚገኙ ስደተኞች እና ጥገኝነት ጠያቂዎች ጥበቃ እና ድጋፍ በማስተባበር ጉዳይ ላይ በዋነኝነት ኃላፊነት ያለበት ተቋም የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. የስደተኞች እና ተመላሾች አገልግሎት ሲሆን የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት (ተ.መ.ድ.) የስደተኞች ከፍተኛ ኮሚሽነር መንግሥት ለስደተኞች እና ጥገኝነት ጠያቂዎች የሚያደርገው ጥበቃ እና ድጋፍ የተሟላ እንዲሆን በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ድጋፍ እንዲያደርግ ኃላፊነት ተጥሎበታል፡፡ በኢትዮጵያ ለሚገኙ ስደተኞች እና ጥገኝነት ጠያቂዎች በመንግሥት እና በተ.መ.ድ. የስደተኞች ከፍተኛ ኮሚሽነር ከሚደረገው ጥበቃ በተጨማሪ በተለያዩ ዓለም አቀፍ እና ሀገር በቀል የተራድዖ ድርጅቶች ድጋፍ ይደረጋል፡፡

ኢትዮጵያ በአፍሪካ ከፍተኛ ቁጥር ያለው የስደተኛ ማኅበረሰብ ከሚያስተናግዱ ሀገራት አንዷ ስትሆን በኢትዮጵያ የሚገኙ ስደተኞች እና ጥገኝነት ጠያቂዎች አብዛኛዎቹ ከደቡብ ሱዳን፣ ሱማሊያ፣ ኤርትራ፣ ሱዳን፣ ሶሪያ፣ የመን፣ ዴሞክራቲክ ሪፐብሊክ ኮንጎ የመጡ ናቸው፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ በሥራ ላይ ያሉ 22 የስደተኞች መጠለያ ጣቢያዎች የሚገኙ ሲሆን፤ በአፋር፣ በቤንሻንጉል ጉሙዝ፣ በጋምቤላ እና በሶማሌ ክልሎች ከፍተኛ ቁጥር ያላቸውን ስደተኞች እና ጥገኝነት ጠያቂዎች የያዙ መጠለያዎች ይገኛሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በሶማሌ እና በአማራ ክልሎች 2 የስደተኞች ሳይቶችም ይገኛሉ፡፡

ኮሚሽኑ ከ2014 ዓ.ም. እስከ 2015 ዓ.ም. በጀት ዓመት ባለው ጊዜ ውስጥ ከ650,000 በላይ ስደተኞችን እና ጥገኝነት ጠያቂዎችን የሚያስጠልሉ 17 መጠለያዎችን፣ ሳይቶችን፣ መቀበያ ጣቢያዎችን እና የከተማ ስደተኞችን በ4 ክልሎች እና በአንድ ከተማ አስተዳደር በክትትል ሥራዎቹ ለመሸፈን ችሏል፡፡ በዚህ ክትትል መሠረት መንግሥት ስደተኞችን ተቀብሎ እያስተናገደ መሆኑን፣ በተለይም በሱዳን የተቀሰቀሰውን ግጭት ተከትሎ ወደ ኢትዮጵያ የገቡ ስደተኞችን በመቀበል እና በማስተናገድ ላይ መሆኑን፣ እንዲሁም ከሱማሊያ ላስአኖድ በግጭት ምክንያት ወደ ኢትዮጵያ የገቡ ስደተኞችን በመቀበል ላይ መሆኑን፣ በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ የሚገኙ ስደተኞች ላይ በተለይም ከግንቦት ወር 2015 ዓ.ም. ጀምሮ ከሕግ አግባብ ውጭ ሲከናወን የነበረው እስር መሻሻል ማሳየቱን፣ ከአፋር ክልል በራሃሌ የስደተኞች መጠለያ ጣቢያ በሰሜኑ ጦርነት ምክንያት ወደ ተለያዩ ስፍራዎች ሸሽተው የነበሩ

ስደተኞች በሕወሓት እና በፌዴራል መንግሥት መካከል የሰላም ስምምነት መደረጉን ተከትሎ ወደ መጠለያ ጣቢያዎች እንዲመለሱ መደረጉን፣ የትምህርትና የጤና አገልግሎት አቅርቦትን ጨምሮ የተለያዩ ድጋፎች ለስደተኞች የሚደረጉ መሆኑን፣ ስደተኞች በተለያዩ ሥራዎች ላይ በመሰማራት በኢኮኖሚ እራሳቸውን እና ቤተሰባቸውን የሚደግፉበት ሁኔታ መኖሩን እንደ ዋና ዋና ቁልፍ እመርታዎች ለይቷል።

በኢትዮጵያ የሚገኙ ስደተኞች ከስደተኞች ምዝገባ፣ ከስደተኝነት ሁኔታ አወሳሰን እንዲሁም ሰነድ የማግኘት መብት ጋር ተያይዞ የሚስተዋሉ ክፍተቶች በመኖራቸው ምክንያት ስደተኞች እና ጥገኝነት ጠያቂዎች ለተለያዩ የመብት ጥሰቶች ይጋለጣሉ። ምዝገባ ያልተደረገላቸው ስደተኞች እና አዲስ የተወለዱ ሕፃናት የሰነድ ማስረጃ ባለማግኘታቸው እንዲሁም የስደተኝነት ሁኔታ ያልተወሰነላቸው ጥገኝነት ጠያቂዎች የሰብአዊ ድጋፍን ጨምሮ ሌሎች አገልግሎቶችን እንደማያገኙና የዕለት ተዕለት ኑሮአቸውን የሚመሩትም በሌሎች ስደተኞች እርዳታ መሆኑ፣ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. የስደተኞችና ተመላሾች አገልግሎት ላለፉት ሦስት ዓመታት በአዲስ አበባ የሚገኙ ጥገኝነት ጠያቂዎችን ምዝገባ ያቋረጠ መሆኑ እና በተለይም በአዲስ አበባ የሚገኙ ኤርትራዊያን ምዝገባ ለማድረግ እንዳልቻሉ፤ ይሁንና ይህ ሪፖርት በሚዘጋጅበት ወቅት የስደተኞች እና ተመላሾች አገልግሎት ለስደተኞች መታወቂያ እድሳት እና አዲስ መታወቂያ መስጠት መጀመሩን ያሰወቀ ቢሆንም በአዲስ አበባ ውስጥ የሚገኙ ጥገኝነት ጠያቂዎች ምዝገባ ይህ ሪፖርት እስከወጣበት ጊዜ ድረስ እንዳልተጀመረ ለኮሚሽኑ አሳውቀዋል። ከዚህም ጋር ተያይዞ በነጻነት የመንቀሳቀስ መብታቸው መገደቡ፣ የሰነድ ማስረጃ የላችሁም በሚል ምክንያት ለእስር መዳረጋቸው፤ ከሁለት መቶ በላይ የሚሆኑ ኤርትራዊያን ተገደው በሕይወታቸው ላይ አደጋ ሊደርስ ይችላል ብለው ወደሚሰጉበት የመጡበት ሀገር ኤርትራ እንዲመለሱ መደረጉ ከዋና ዋና አሳሳቢ ጉዳዮች ውስጥ የሚጠቀሱ ናቸው።

የስደተኞችን ጸጥታ እና ደኅንነት በሚመለከት በኢትዮጵያ የሚገኙ ስደተኞች፣ ከተቀባይ ማኅበረሰብ ጋር በሚከሰቱ ግጭቶች የሚደርስባቸው ጉዳት፣ የደኅንነት ሥጋት እና በጦርነቶች ምክንያት በታጣቂዎች በደረሱባቸው ጥቃቶች የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች ተፈጽመውባቸዋል።

ኮሚሽኑ የስደተኞች የመዘዋወር ነጻነት በተለያዩ ምክንያቶች የተገደበባቸው ሁኔታዎች መኖራቸውን ለማወቅ ችሏል። በተለይም የመታወቂያ ካርድ አገልግሎት በመቋረጡ ምክንያት የተወሰኑ ስደተኞች ከቦታ ቦታ ሲንቀሳቀሱ ለእስር መዳረጋቸውን ለማወቅ ተችሏል። በተጨማሪም ሕጋዊ ሰነዶችን ለማግኘት ከሚፈጠረው ችግር የተነሳ የተወሰኑ ስደተኞች ከአንድ ከተማ ወደ ሌላ ከተማ ለመንቀሳቀስ በሚያደርጉት ጥረት በተለያዩ ሕገ ወጥ ድርጊቶች (ለምሳሌ ሀሰተኛ የቀበሌ መታወቂያ፣ ሀሰተኛ የሪፌራል ሕክምና ወረቀት መጠቀም) ውስጥ ገብተው እንደሚገኙ፤ ይህም ለእስር እንደሚዳርጋቸው ለማወቅ ተችሏል። በአዲስ አበባ የሚገኙ የከተማ ስደተኞች ውስጥ መታወቂያቸው ባለመታደሱ ምክንያት ከቦታ ቦታ በነጻነት የመንቀሳቀስ መብታቸው ከመገደቡም ባሻገር ለእስራት የተጋለጡ ሲሆን ከመታወቂያ ካርድ አገልግሎት በተጨማሪ የወሳኝ ኩነት ምዝገባ አገልግሎት በመቋረጡ ምክንያት ከኢትዮጵያ ውጭ ወደ ሦስተኛ ሀገር ለመጓዝ እንዳልቻሉ፤ በጋምቤላ ክልል በሚገኙ የደቡብ ሱዳን ስደተኞች በተለያየ ጊዜ በሚከሰት ግጭት የመንቀሳቀስ እና ከቦታ ቦታ የመዘዋወር መብታቸው መገደቡን ለመገንዘብ ተችሏል።

ስደተኞች ፍትሕ የማግኘት መብታቸው በተለያዩ ምክንያቶች እየተጣሰ መሆኑን፣ ከነዚህም በዋናነት የተለዩት አብዛኛዎቹ የስደተኛ መጠለያ ጣቢያዎች ከከተማ ርቀው የሚገኙ በመሆናቸውና በሁሉም የመጠለያ ጣቢያዎች ተዘዋዋሪ ችሎት (Mobile Court) ባለመድረሱ ጉዳያቸውን በሕግ ወደ ተቋቋመ ፍርድ ቤት ለመውሰድ እንደሚቸገሩ፣ በአብዛኛዎቹ መጠለያ ጣቢያዎች ስደተኞች ነጻ የሕግ ድጋፍ አገልግሎት እንደማያገኙ፣ የሕግ ግንዛቤያቸውን እና ንቃታቸው እንዲዳብር የሚሰጡ ስልጠናዎች አነስተኛ መሆናቸው ለመረዳት ተችሏል፡፡
ለስደተኞች እና ጥገኝነት ጠያቂዎች የሚደረግ የሰብአዊ ድጋፍን በሚመለከት የምግብ ድጋፍ አቅርቦት ከግንቦት ወር 2015 ዓ.ም. ጀምሮ ሙሉ ለሙሉ ተቋርጦ በቆየባቸው ወራት አቅርቦቱ እስከቀጠለበት ጊዜ ድረስ ስደተኞች ለከፋ የሰብአዊ ቀውስ መዳረጋቸውን ኮሚሽኑ ተገንዝቧል። ለስደተኞች የሚደረግ የጤና አገልግሎትን በሚመለከት አብዛኛው የስደተኛ መጠለያ ጣቢያዎች የመድኃኒት፣ የሕክምና መሣሪያዎች፣ የላብራቶሪ እና የመታከሚያ አልጋዎች እጥረት መኖሩን ለማየት ተችሏል፡፡

ለጥቃት ተጋላጭ ለሆኑ ማኅበረሰቦች የሚደረግ ልዩ ድጋፍን በሚመለከት ሕፃናት፣ ሴቶች፣ አረጋውያን እና አካል ጉዳተኛ ስደተኞች እና ጥገኝነት ጠያቂዎች ድጋፍ ለማድረግ የተወሰኑ ጥረቶች እንዳሉ፣ ነገር ግን የሚደረግላቸው ድጋፍ የተለየ ፍላጎታቸውን፣ ዕድሜአቸውን እና የአካል ጉዳታቸውን ከግምት ውስጥ ያስገባ አለመሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

ለስደተኞች በዋነኝነት የሚቀርቡ ዘላቂ መፍትሔዎችን ተግባራዊ ለማድረግ የተለያዩ ተግዳሮቶች የሚገጥሙ ሲሆን በተለይም ያደጉ ሀገራት ስደተኞችን ለመቀበል ያላቸው ፍላጎት ዝቅተኛ በመሆኑ፣ ስደተኞች በፍቃደኝነት ወደ ሀገራቸው እንዳይመለሱ አብዛኛዎቹ ስደተኞች የመጡበት ሀገራት ለስደት የዳረጋቸው ምክንያት ባለመቀየሩ እና ከተቀባይ ማኅበረሰብ ጋር ተቀላቅለው እንዳይኖሩ በኢትዮጵያ ያለው የኢኮኖሚ ሁኔታ አስቻይ ባለመሆኑ ሦስቱንም የዘላቂ መፍትሔዎች ማሳካት አዳጋች እንደሆነ ለመረዳት ተችሏል፡፡

**ምክረ ሐሳብ**

**ምዝገባ፣ ሰነድ ማግኘት እና የስደተኝነት ሁኔታ አወሳሰንን በተመለከተ**

- በአዲስ አበባ ከሦስት ዓመታት በላይ ተቋርጦ የቆየው የስደተኞች ምዝገባ በአፋጣኝ እንዲቀጥል፤
- በአዲስ አበባ ውስጥ ለሚገኙ የከተማ ስደተኞች ላለፉት ሦስት ዓመታት ተቋርጦ የነበረው የመታወቂያ እድሳት መጀመሩ መልካም እመርታ መሆኑን ኮሚሽኑ የሚገነዘብ ሲሆን፤ በሁሉም መጠለያ ጣቢያዎች ውስጥ ለሚገኙ ስደተኞች በተመሳሳይ ሁኔታ ይህ የመታወቂያ እድሳት እና አዲስ መታወቂያ የመስጠት አገልግሎት በአፋጣኝ እንዲቀጥል፤
- የስደተኝነት ሁኔታ ሳይከናወንላቸው ለዓመታት የቆዩ ጥገኝነት ጠያቂዎች የስደተኝነት ሁኔታ አወሳሰን እንዲከናወንላቸው፤
- መንግሥት የስደተኞችን መታወቂያ ወደ ዲጂታል መታወቂያ ለመቀየርና ለማዘመን እያደረገ ያለው ጥረት የሚበረታታ ሲሆን፤ ሥራው ተጠናክሮ የስደተኞች የመረጃ አያያዝን፣ የመታወቂያ አሰጣጥን እና የወሳኝ ኩነት ምዝገባን በማሻሻል እና በማዘመን በሥርዓቱ ላይ ያለውን ክፍተት እንዲቀርፍ።

**የጸጥታና ደኅንነት እና የመንቀሳቀስ መብቶችን በተመለከተ**

- ስደተኞች የሚገኙባቸውን መጠለያ ጣቢያዎች ጸጥታ እና ደኅንነት ማረጋገጥ፣ በተለይ መጠለያዎቹ የሲቪል ባሕርይ እንዲኖራቸው ተገቢ እርምጃ እንዲወሰድ፤
- በስደተኞች እና በተቀባይ ማኅበረሰብ መካከል ግጭት ባለባቸው የስደተኛ መጠለያ ጣቢያዎች መንግሥት ከሌሎች አጋር አካላት ጋር በመሆን የግጭት መንስዔዎችን በመለየት እና ለጉዳዩ ዕልባት በመስጠት ሁለቱን ማኅበረሰቦች የሚያቀራርብ ሥራ እንዲሠራ፤ በተጨማሪም የግጭቶችን መንስዔ በማጣራት ግጭቶች ከመከሰታቸው በፊት ተገቢ የሆነ የመከላከል ሥራ እንዲሠራ፤
- በመጠለያ ጣቢያዎች በሴቶች ላይ የሚደርሰውን የጾታ ጥቃት ለማስቆም የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራን ጨምሮ የመከላከል ሥራዎች እንዲሠሩ፤ ድርጊቱን በሚፈጽሙ ግለሰቦችም ላይ የሕግ ተጠያቂነትን ማረጋገጥ፤
- በስደተኞች ላይ የሚደረግን እገታ ማስቆም እንዲሁም የጸጥታ እና ደኅንነት መብትን በሚጥስ ተግባር ላይ ተሳታፊ የሆኑ ግለሰቦችን ወይም አካላትን ተጠያቂ በማድረግ የስደተኞችን ፍትሕ የማግኘት መብትን ማረጋገጥ።

**ፍትሕ የማግኘት መብትን በሚመለከት**

- መንግሥት ስደተኞች በዓለም አቀፍ እና በብሔራዊ ሕጎች በተሰጣቸው መብት መሠረት ፍትሕ የማግኘት መብታቸው እንዲከበር እና ነጻ የሕግ ድጋፍ አገልግሎት እንዲያገኙ እንዲያደርግ፤
- ስደተኞች የፍትሕ ተቋማትን ለመገልገል የሚያስችሉ የቋንቋ፣ የሕግ ዕውቀት እና የገንዘብ ተግዳሮቶች እንዳይገጥሟቸው ድጋፍ እንዲደረግላቸው።

**የሰብአዊ ድጋፍና የማኅበራዊ አገልግሎቶች አቅርቦት ጋር በተያያዘ**

- ተቋርጦ የነበረው የምግብ ድጋፍ ይህ ሪፖርት በወጣበት ወቅት የቀጠለ ቢሆንም አሁንም የሚቀርበው የምግብ ድጋፍ በቂ ባለመሆኑ በስደተኞች የሰብአዊ መብቶች አያያዝ ላይ እያስከተለ ያለውን ተጽዕኖ ለመቅረፍ በቂ፣ ወቅቱን የጠበቀ እና ተደራሽ የሆነ የምግብ ድጋፍ እንዲደረግ፤

- ለሕክምና እና ለትምህርት መስጫ ተቋማት አስፈላጊውን ግብአት በማሟላት ለስደተኞች በቂ እና የተሟላ አገልግሎት እንዲሰጡ ማድረግ፤ ለዚህም መንግሥት የጉዳዩን አሳሳቢነት ለድጋፍ ሰጪ ድርጅቶች በማሳወቅ የገንዘብና የቁስ ድጋፍ እንዲያሰባስብ፤
- መጠለያ፣ ንጹሕ የመጠጥ ውሃ፤ ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶች ድጋፍ (ፍራሽ፣ ብርድ ልብስ፣ የማብሰያና የመመገቢያ ቁሳቁሶችን የመሳሰሉ) ለስደተኞች እንዲሟሉ፤
- በሰሜኑ ጦርነት ምክንያት በትግራይ፣ በአፋር እና በአማራ ክልሎች የሚገኙ ስደተኞች ለገጠማቸው የሥነ-ልቦና ጉዳት ተገቢው የሥነ-ልቦናና ማኅበራዊ ድጋፍ እንዲደረግ፤
- ለስደተኞች እና ጥገኝነት ጠያቂዎች መሠረታዊ አገልግሎቶችን ለሚሰጡ ተቋማት የስደተኞችን መብቶች በሚመለከት ግንዛቤ የማስጨበጥ ሥራ በመንግሥት እና በተራድዖ ተቋማት እንዲከናወን።

## ለመብት ጥሰት ተጋላጭ ለሆኑ ስደተኞች የሚደረግ ድጋፍን በተመለከተ

- መንግሥት እና የተራድዖ ተቋማት የሚያቀርቧቸው የሰብአዊ ድጋፍ ለሴቶች፣ ሕፃናት፣ አካል ጉዳተኛ እና አረጋዊያን ለሆኑ እንዲሁም በአጠቃላይ ልዩ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ስደተኞች ተደራሽ መሆኑን እንዲያረጋግጡ፤
- ለሕፃናት ዕድሜአቸውንና ልዩ ፍላጎታቸውን መሠረት ያደረገ ምግብ እና ሕክምናን ጨምሮ ልዩ ድጋፍ እንዲደረግላቸው፤
- ለአካል ጉዳተኛ እና አረጋውያን ስደተኞች ልዩ ፍላጎቶቻቸውን ከግምት ውስጥ ያስገባ ድጋፍ በመንግሥት እና በተራድዖ ተቋማት እንዲደረግላቸው፤
- ለሴት ስደተኞች የንጽሕና መጠበቂያ ቁሳቁሶች እንዲሁም የሥነ-ተዋልዶ ጤና አገልግሎቶችን ጨምሮ ልዩ ፍላጎታቸውን ባገናዘበ መልኩ ሰብአዊ ድጋፍ እንዲደረግላቸው።

## ዘላቂ መፍትሔን በሚመለከት

- ኢትዮጵያ ሁሉን አቀፍ የስደተኞች ምላሽ ማዕቀፍን ለመተግበር ስትወስን የዓለም አቀፉን ማኅበረሰብ ድጋፍ ተስፋ በማድረግና አጋር ተቋማትም ድጋፍ ለማድረግ መተማመኛ ቃላቸውን በመስጠታቸው ነው። ስደተኞች በሥራ ላይ እንዳይሰማሩ የፋይናንስ እጥረት ትልቁ ማነቆ በመሆኑ ይህንኑ ጉዳይ ለዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ በማሳወቅ መንግሥት አስፈላጊውን የፋይናንስ ድጋፍ እንዲያሰባስብ፤
- ስደተኞች በተለያዩ ሥራዎች ላይ በመሰማራት በኢኮኖሚ እራሳቸውን እና ቤተሰባቸውን የሚደግፉበትን ሁኔታ ለማመቻቸት መንግሥት እና ተራድዖ ድርጅቶች የበኩላቸውን ድጋፍ እንዲያደርጉ፣ ለስደተኞች የእርሻ መሬት፣ የእርሻ ግብአት እንዲቀርብ ማድረግ እና ይህንን በሚመለከትም የተቀባይ ማኅበረሰብን አመለካከት በአወንታዊ መልኩ የሚቀይር የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ እንዲሠራ፤ እንዲሁም የስደተኞች ወደ ሦስተኛ ሀገር መሻገር ሁኔታ በሦስተኛ ሀገር መልካም ፈቃድ ላይ የተመሠረተ እና ዕድሉም በጣም ጠባብ በመሆኑ፤ ስደተኞች ይህን ተገንዝበው ሌሎች ዘላቂ አማራጮች ላይ በማተኮር የመፍትሔ አካል እንዲሆኑ መንግሥትና የተ.መ.ድ የስደተኞች ከፍተኛ ኮሚሽነር ተገቢውን ግንዛቤ ማስጨበጫ እና የቴክኒክ ድጋፍ እንዲያደርጉ።